# የሰረቁት ስጋ ያስይዛል መረቁ
(የሐማ ቱማ ድብቅ ሴራ)




በወያኔ ኢህዴግ "ተቃዋሚነታቸው" ለረዥም ዘመናት የሚታወቁት የአቶ እያሱ አለማየሁ መጽሃፍ ባላንጣዎቼ የሚሏቸው ባለስልጣናት በተገኙበት በዋቢ ሸበሌ ሆቴል መመረቁ ተሰማ፡፡

The Case of the Socialist Witch doctor በመባል የሚታወቀው የአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ መጽሐፍ የሶሻሊስቱ ጠንቋይ ጉዳይ በሚል ርዕስ በአማርኛ ተተርጉሞ አዲስ አበባ ውስጥ December 27, 2014 ቀን የወያኔ ባለሥልጣናት በተገኙበት በዋቢ ሸበሌ ሆቴል ተመርቋል።

የመፅሀፉን በኣዲስ ኣበባ መታተምና በተለይም የወያኔ ቱባ ባለሰልጣናትና ጀሌዎቻቸው ዋና መናኸሪያ በሆነው በዋቢሸበሌ ሆቴል መመረቁን አስመልክቶ ለተነሳው ጥያቄ አቶ ኢያሱም ሆኑ በእሳቸው የሚመራው "ኢሕአፓ" ምንም ዓይነት መግለጫ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም ። እንደውም ይባስ ብለው በደጋፊዎቻቸው ድህረ ገጾች የመጸሐፉን ግምገማ አሰራጭተውት ይገኛል።

ስለ ዋቢ ሸበሌው ዝግጅት ይህንን ድረ ገጽ ይመልከቱ። http://www.borkena.com/2014/12/27/the-case-of-the-socialist-witchdoctor/

ኢሕአፓን በመከፋፈልና አባላትን ወያኔ እያለ በመፈረጅ የሚታወቁት አቶ ኢያሱ ከወያኔ ጋር እንዲህ የቀረበ ግንኙነት ሊመሠርቱ ይችላሉ ተብሎ አይገመትም ነበር። ይሁንና ዛሬ ጽዋው ሞልቶላቸው ፓሪስ አገር በምትኖር አንዲት ጋዜጠኛ አማካኝነት ድርድር እንዳደረጉና እንደተሳካላቸውም ይነገራል። አቶ እያሱ ይህን ሲያደርጉ መቸም ያምራል ብለው ለነብር ልጅ እዳሩ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይሁን እንጅ ወያኔ የነጻውን ፕረስ ሰዎች ፣ ታጋዮችን ከውጭ ሳይቀር እያፈነ በሚያስርበት በአሁኑ ወቅት አቶ ኢያሱ መጽሐፍ እያተሙ መሐል አራዳ አዲስ አበባ ላይ ሲሸጡ መታየቱ አጀብ ከማለት ውጭ ሌላ ምን ይባላል። መቸም አንዳች የውስጥ ነገር የድርጅት ሥራ! እንደሚባለው አይነት ስምምነት ቤጤ! ሳይኖር በትግል የተገኘ ድል ነው ማለት ከቶ አይታሰብም። ሳይሰድብህ ስደበው፣ በሚል ዘዬ አቶ ኢያሱ "እንጻፍ ከተባለማ" በሚል ጽሁፋቸው ሁሉን ወያኔ ሲሉ ከርመው ዛሬ በዋቢ ሸበሌ ሆቴል መጽሐፍ ማስመረቃቸው ሲሰማ ምን ሊሆን እንደሚችሉ መገመት ከቶ አያዳግትም።

ቀደም ሲል ከወያኔ ጋር ባደረጉት ስምምነት መሰረት የመጽሐፉ ህትመትና ምረቃ እንዳይደናቀፍ በማሰብ በባሕር ዳር የተደረገውን የንፁሃን ዜጎቸ ጭፍጨፋ የሚያወግዝ መግለጫ ድርጅታቸው "ኢ.ሕ.አ.ፓ" እንዳያወጣ አቶ ኢያሱ እስከአሁን ድረስ ማገዳቸው

ለአብነት የሚጠቀስ ዋቢ ነው። ይህንን በሚመለከት በድህረ ገጻቸው መመልከት ይቻላል። ለዜጎች ደህንነትና መብት ሲታገል የኖረና አያሌ መስዋእትነት የከፈለበትን አብይ ሀገራዊና ህዝባዊ ዓላማ ዛሬ በአንፃራዊነት ወደጎንን ገለል የመደረጉና ዜጎች ያለአግባብ በዘረኞች ሲጨፈጨፉና ሲገደሉ ማውገዝ እንኳን ያልተቻለበት ሁኔታ ላይ መደረሱ፤ ወያኔ የሚፈፅመዉን አይነተኛ የግፍ ተግባር ከመደገፍ ያለፈ ሌላ ምን ሊባል ይቻላል? በተለይ በእያሱ የሚመራው “ “ኢሕአፓ” ደጋፊዎች ይህንን በተመለከተ ምንም ተቃውሞ አለማሰማታቸው በብዙዎች ዘንድ አግራሞትን ፈጥሯል። በቅርቡ የኢያሱ “ኢሕአፓ” የቡርኪና ፋሶን ትግል ይደግፋል” የሚል መግለጫ እንዳላወጣ ሁሉ፣ በባሕር ዳር ለተጨፈጨፉት ኢትዮጵያዉያን ወገኖች አንዲት ቅንጣት መግለጫ ማውጣት የተሳነው ድርጅት ሆኖ የመገኘቱ ጉዳይ፣ ከባህርዳር ይልቅ የቡርኪ ናፋሶ ጉዳይ ያሳሰበው ይመስላል።

የእነ ጸጋዬ ደብተራውን፣ የነ ጋይም፣ የነ ይሰሃቅ ደብረፅዮን፣ የነ ስጦታው ሁሴን ወዘተ ገዳይ ከሆነው ወያኔ ጋር ለአንድ መጽሐፍ ተብሎ እየተሞዳሞዱ የዜጎችን ገሀድ የወጣ ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ ማውገዝ አለመቻል ለኢ.ሕ.አ.ፓ ለዘመናት በታጋዮቹ ደም የገነባውን ዝናና ክብር ከማቆሸሹም ባሻገር፣ ሃገርና ሕዝብን የመካድ አይነት አሳፋሪ ተግባርም ጭምር ነው የሚሆነው። “ በኢሕአፓ” ስም መነገድ ካሁን ወዲያ ማክተም አለበት ። ከአቶ ኢያሱ ጋር በመወገን በተሳሳተ መስመር ያላችሁ ይህ ጥያቄ መልስ እስካላገኘ ድረስ ራሳችሁን ከዚህ የክህደት አባዜ ነፃ መሆን ከቶ አትችሉም። ድርጅቱንም ሆነ ትግሉን አዘቅት ውስጥ ከማስገባታችሁ በፊት ላፍታ ቆም ብላችሁ ራሳችሁንንና ሥራችሁን ትፈትሹ ዘንድ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ትጠየቃላችሁ።

አቶ እያሱ በድርጅቱ ውስጥ እንዳሻው ሲፏልሉ የመኖራቸውን ያህል በአሁኑ ወቅት ደግሞ እየተንዘባዘቡ የድርጅቱን ዓላማ በመጣስ ህልውና በሚፈታተን ተግባር ላይ ተሰማርተው የመገኘታቸው ጉዳይም ሆነ የለዘብተኝነት አቋም ካላቸው ጋሻጃግሬዎች አንፃር ሲመዘን ፦

“ እረ’ ምን ሞኝ ነው፡ እረ’ ምኑ ጅል ነው፤
  ሲሰድቡት ዝም ያለ ቢመቱትም ያው ነው።” …. የሚያሰኝ ሆኗል።

የአቶ እያሱ አለማየሁ ያሻቸው በድርጅት መሪነት እንዲያም ሲል በተራ አባልነት እየተሰየሙ በተለያዩ ድህረ -ገፆችና ሚዲያዎች በርካታ ነጥቦች እያነሱ እንዲህና እንዲያ ሲዘላብዱ መቆየታቸው ይታወቃል። ከዛም ባሻገር ሲፈልጉ በስማቸው አለያም በብዕር ስሞች ብዙ ጉዳዮችን ሲያስደምጡን ኖረዋል፡፡ በአለፈው ዓመት በጠንካራ የኢህአፓ አባላት ጥረት በጉባኤ እስከሚወሰን ድረስ የታገዱ መሆናቸው ቢታወቅም፣ አሁን ደግሞ በማናለብኝነት እንዲህ ያለ የንቀትን የክህደት ተግባር በይፋ መፈፀማቸው የኢ.ህ.አ.ፓን ግብዓተ መሬት ለማፋጠን ቆርጠው የተነሱ ይመስላል፡፡

አቶ ኢያሱ የኢህአፓ አባላትን እየከፋፈሉና እርስበርስ እያጋጩ ድርጅቱ ኣሁን ካለበት ደረጃ ማድረሳቸው ብቻ ሳይበቃቸው ህልውናዉን ለማጥፋት የተቻላቸውውን ያህል ኣድርገዋል እያደረጉም ነው ማለት ይቻላል።   የኢህአፓ በጠንካራ አባላት ገንዘብ የቆመ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን፡ አባላቱ ድጋፍ ከመስጠትና ገንዘብ ከማዋጣት በስተቀር በድርጅቱም ይሁን በአመራሩ ዙሪያ ምንም ዓይነት ጥያቂዎችን እንዳያነሱ ሰንጎ በመያዝ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከዚያም አልፎ ደፍረው ወሳኝ ጥያቄ ያነሱ ጠንካራ አባላትን ክድርጅቱ እንዲባረሩ እስከማድረግም የደረሰ ሰው ነው።  ከድርጅቱ ሕገ - ደንብ ውጭ በስሙና ደጋፊ ጀሌዎቹ በሆኑ ድህረ ገጾች እየታገዘ የማይታወቅ መስሎት የበርካታ ነባር የታጋዮችን ስም ሲያጎድፍና

ሲያጥላላ መቆየቱ ይታወቃል። ተስፋ የተጣለበት የታሪክ ተረካቢውና የድርጅቱ የጀርባ ኣጥንት የሆነውን የወጣት ክንፍ የኣመራር አባላትን እስከማባበር የደረሰ እብሪተኛና ኢዲሞክራት ነው። አሁን በስተመጨረሻ ደግሞ እየታየ ያለው ትንግርታዊ ድራማው፣ ይህንን ሁሉ ወንጀል በምን አግባብ እንደሠራውና እየሠራው እንዳለ በሸንጎ ይፋ ያደረገበት የሰሞኑ ያዲስ አበባው የዋቢ ሸበሌ ሆቴል ትእይንት የሁላችንም መነጋገሪያ ለመሆን በቅቷል። የግለሰቡን ወቅታዊ አቋም ለመገመት ከዚህ የበለጠ ማስረጃ መጥቀስ የሚያሻው ጉዳይ አይመስለኝም።

“የክረምት በቆሎ ጎርፍ የደፈጠጠው፣
ተኝቶ ያፈራል ትል እያላመጠው ።” .... እንዳይሆንና እንዳንተዛዘብ።

ቤቱማ ምን’ አርጎ፡ የበላንበቱ፡ የጠጣንበቱ፤
አልጋው ይፍረስ እንጅ፡ ትኋን ያለበቱ። .... ያለው ያአገሬ ገበሬ ወዶ እንዳልሆነ ልብ ይሏል!

ወደፊት አቶ ኢያሱ በኢሕፓና በአባላቱ ላይ የፈጸመውን ወንጀል በማስረጃ የተደገፈ ዶክመንት አንደማቀርብ ቃል አየገባሁ በዚህ ልሰናበታችሁ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል

ኢሕአፓ አንድ ይሆናል!

# ዳግማዊ ጋይም -